City of Seattle

# መድሎን ያለመፈጸም ማሳሰቢያ

የሲያትል ከተማ (ከተማ) በ Title VI of the Civil Rights Act of 1964 (በ1964ቱ ሲቪል መብቶች ድንጋጌ አርእስት VI)፣ በ Civil Rights Restoration Act of 1987(P.L. 100.259, በ1987ቱ ሲቪል መብቶች መመለሻ ድንጋጌ)፣ the Age Discrimination Act of 1975(በ1975ቱ የዕድሜ መድልዎ ድንጋጌ) በተሻሻለው እንዲሁም Title II of the American with Disabilities Act (አካል ጉዳት ያለባቸው አሜሪካውያን ድንጋጌ አርእስት II) መሰረት ማንኛውም ሰው በዘር, በቀለም, በብሄር, በሃይማኖት, በጾታ, በዕድሜ, ወይም በአካል ጉዳት ላይ ተመስርቶ በከተማ ፕሮግራሞች እና ተግባራት ላይ አድልዎ እንደማይፈጸምበት ያረጋግጣል። በተጨማሪም ከተማው በSeattle Municipal Code(የሲያትል የማዘጋጃ ቤት ድንጋጌ) 14.04, 14.06 እና 14.10 በቀረበው መሰረት ሌሎች ተጨማሪ የስቴት እና የማዘጋጃ ቤት የሲቪል መብቶች ሕጎችን እንደሚያከብር እንዲሁም አንድም ሰው በፆታ ዝንባሌ፣ በፆታ ማንነት፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በወላጅች ሁኔታ፣ በፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም፣ በሃይማኖት፣ በዘር፣ በSection 8 housing program (Section 8 የቤቶች ልማት ፕሮግራም) ውስጥ ባለው ተሳትፎ፣ በወታደራዊ አቋም ወይም የውትድርና ሁኔታ ወይም በሕዝብ ቦታ ላይ ጡት በማጥባት ላይ በተመሰረተ በፕሮግራሞቹ እና ተግባራቱ ውስጥ አድልዎ እንደማይፈጸምበት ያረጋግጣል።

ማንኛውም ሰው በ Title VI ወይም በሌሎች ህጎች ስር ከለላ ያለው መድልዎ ተፈጽሞብኛል የሚል ስሜት ካለው አቤቱታውን ወደ Seattle Office for Civil Rights (የሲያትል ሲቪል መብቶች ጽ/ቤት) ማስመዝገብ ይችላል።

በ City of Seattle Title VI program (የሲያትል ከተማ የ Title VI ፕሮግራም) ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወይም እንዴት አቤቱታ ማስመዝገብ እንደሚቻል መረጃ ለማግኘት የ Seattle Office for Civil Rights (የሲያትል ሲቪል መብቶች ጽ/ቤት)ን በ (206) 684-4500 ያናግሩ፣ በ ocr_intake@seattle.gov ኢሜል ያድርጉ፣ www.seattle.gov/civilrights ድረ ገጽ ይጎብኙ ወይም በአካል  በ810, Third Avenue, Suite 750, Seattle, WA 98104 ይጎብኙ። የ Seattle Office for Civil Rights (የሲያትል ሲቪል መብቶች ጽ/ቤት) ከሰኞ እስከ አርብ ከ 8am እስከ 5pm ድረስ ክፍት ነው።